የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No 21
ADDIS ABABA, 23th January 2018.


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲ ዓ.ም

የደን ልማት ፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ...............................................ገጽ ፲ሺ፷፰


**CONTENT**


Proclamation No. 1065/2018

Forest Development, Conservation and Utilization Proclamation……………………………Page 10068


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲

## የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ

የደን ዘርፈ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም ትልቅ ሚና የሚጫወት በመሆኑና በሀገራችን በከፍተኛ ደረጃ በደን መመናመን ምክንያት እየተከሰተ ያለውን አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመግታት ዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ፤

እየተከሰተ ያለውን የአፈር መከላት፣ የበረሃማነት መስፋፋትና የብዝሐ ሕይወት መመናመን ለመግታት የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፤

የደን ዘርፉ የህብረተሰቡን የደን ውጤት ፍላጎትና አቅርቦት ልዩነት ለመሙላት፣ የግብርና ምርት እድገትን በማስቀጠል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ፤

መንግስት ለዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና እና ስትራቴጂዎች ለማስፈጸም በመንግስት እና በግል ባለቤትነት ከሚለማው ደን በተጨማሪ የማህበረሰብና የማህበራት ባለቤትነትን በማረጋገጥ በህብረተሰብ ተሳትፎ ደንን ማልማት ከፍተኛ

## PROCLAMATION No. 1065/2018

## FOREST DEVELOPMENT, CONSERVATION AND UTILIZATION PROCLAMATION

WHEREAS, the forest sector plays an important role in addressing the adverse effects of climate change and sustainable forest development, conservation and utilization plays a crucial role to halt environmental, social and economic problems caused by the high level of forest degradation in the country;

WHEREAS ,forest development, conservation and utilization has a decisive role in preventing soil erosion, desertification and loss of biodiversity;

WHEREAS, the forest sector also has a crucial role in balancing the demand and supply of forest products, sustain agricultural productivity and thereby ensure food security;

WHEREAS ,in addition to developing forest by state and private ownership, it is necessary to introduce community and association forest development to implement the policy and strategy that have

ሚና ያለው መሆኑ ስለታመነበት፣

ለዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ደን ከአካባቢያዊ፤ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አንፃር በምርት ሰጪነት፤ በጥብቅ እንዲሁም በፍፁም ጥብቅ ደንነት መለየትና ማስተዳደር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከዘርፈ ብዙ እና ከሁለትዮሽ ስምምነቶች የደን ዘርፍ ሊያስገኝ የሚያስችላቸውን አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይበልጥ ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በደን ዘርፉ የምርምር፤ የትምህርት፤ የኢንቨስትመንት፣ የግብይት እና የመረጃ ሥርዓትን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፩(፭) እና አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ “ደን” ማለት በደን መሬት፣ በመንገዶች ዳርቻ፣ ወንዝ ዳርቻ፣ በእርሻና የግጦሽ መሬቶች ውስጥና በዙሪያቸው እንዲሁም በመኖሪያ አካባቢዎችና ፓርኮች ውስጥ በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው ወይም በሌላ ዘዴ የለሙ የዛፎችና የዕፅዋቶች እንዲሁም ሌሎች ብዝሃ-ሕይወቶች ክምችት ነው፤

፪/ “የደን ብዝሀ-ሕይወት” ማለት በደን ውስጥ ወይም በደን መሬት ላይ ያለ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የደቂቅ ሕያውን ዝርያዎች ክምችትና ስብጥር በተደጋጋፊነትና በአንድነት የሚገኙበትን ሥርዓተ ምህዳርን የሚያጠቃልል ነው፤

formulated to enhance sustainable forest development, conservation and utilization through to recognizing community ownership and public participation;

WHEREAS, to ensure sustainable forest development, conservation and utilization, it is necessary to classify forest into productive, protected and exclusively protected forests based on their environmental, social and economic significance;

WHEREAS it is necessary to further enhance the environmental, social and economical benefits that may arise from multi-lateral and bilateral agreements;

WHEREAS ,it is necessary to strength forest sector research, education, investment, trade and information system;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 51 (5) and Article 55(1) of the Constitution of the Federal DemocraticRepublic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows.

## SECTION ONE
## GENERAL

### 1.Short Title

This Proclamation may be cited as the “Forest Development, Conservation and Utilization Proclamation No. 1065/2018”.

### 2.Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ “Forest" means trees, plants and other bio-diversity accumulation at and in the surrounding of forest lands, roadsides, riverside, farm and grazing lands as well as residential areas or parks that grow naturally or developed in some other ways;

2/ "Forest biodiversity" means diversity of species of plants, animals and microorganisms and the ecosystem in which they live together in interaction and interdependence in a forest or forest land;

፫/ “ዛፍ” ማለት ዕድሜና መጠን ሳይለይ ማንኛውም የእንጨትነት ባህሪ ያለው ተክል የሚያጠቃልል ሲሆን ቀርከሃ፣ ሸመል፣ ዘንባባና ሚኒስቴሩ የሚሰይማቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን ተክሎችን ይጨምራል፤

፬/ “የደን መሬት” ማለት ለደን ልማትና ጥበቃ ተብሎ የተከለለ ወይም የተሰየመ ማንኛውም መሬት ነው፤

፭/ “የመንግሥት ደን” ማለት በፌደራል እና በክልል መንግሥት ሥር የሚገኝ ማንኛውም ፍጹም ጥብቅ፣ ጥብቅ ወይም ምርት ሰጪ ደን ነው፤

፮/ “የግል ደን” ማለት የመንግስት እና የማህበረሰብ ያልሆነ በማንኛውም የግልና የተቋማት ይዞታ ላይ የሚገኝ ደን ነው፤

፯/ “የማሕበረሰብ ደን” ማለት የአንድ አካባቢ ህብረተሰብ የግል ወይም የወል ይዞታቸውን በጋራ በሚያወጡት ዕቅድ እና ሕገ-ደንብ መሠረት የለማ፣ የተጠበቀ፣ በጥቅም ላይ የሚውል እና የሚተዳደር ደን ነው፤

፰/ “የማሕበራት ደን" ማለት የደን አልሚዎች በማሕበር በመደራጀት የሚያለሙት፣ የሚጠብቁት፣ የሚጠቀሙበት እና የሚያስተዳድሩት ደን ነው፤

፱/ “አሳታፊ የደን አያያዝ” ማለት በመንግስት ደን ውስጥ ወይም ዙሪያ በሚኖሩ ማህበረሰብና መንግስት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት የደን ሀብቱን የማልማት፣ የመንከባከብ፣ የመጠበቅና የመጠቀም መብትን አስመልክቶ የደኑን አስተዳደር የኃላፊነት ሚናን በመለየት ከደኑ የሚገኝን ጥቅም በሚጋሩበት ሥርዓት ላይ በጋራ የሚሰሩበት የደን አስተዳደር ስልት ነው፤

፲/ “ኮንሴሽን” ማለት አንድን የመንግሥት ደን ሀብት ለማልማት፣ ለመጠበቅ ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል ለተወሰነ ጊዜ በውል ህጋዊ ሰውነት ላለው አካል ማስተላለፍ ማለት ነው፤

፲፩/ “ጥብቅ ደን” ማለት ለተለያዩ የሥርዓተ ምህዳር ግልጋሎት የሚውል ደን ሲሆን በሚመለከተው አካል በሚዘጋጅለት የደን ማኔጅመንት ዕቅድ መሠረት የደኑን ዘላቂ ሥርዓተ-ምህዳራዊ ዕሴቶች በማይጎዳ መልኩ በጥቅም ላይ

3/ "Tree" means any woody plant regardless of its age or size and includes bamboo, reed and palms as well as other plants to be designated per se by the Ministry;

4/ "Forest land" means any plot of land demarcated or designated for the purpose of forest development and conservation;

5/ “State forest” means any exclusively, conserved, and productive forest, which is under the ownership of the Federal Government or a Regional State;

6/ “Private forest" means a forest other than State or community, and developed on private or institutions’ holdings;

7/ "Community forest" means a forest developed, conserved, utilized and administered by the community on its private or communal possession based on by laws and plans developed by the community;

8/ “Association forest" means a forest developed, conserved, utilized and administered by associations established to develop forest;

9/ “Participatory forest management" means a forest management approach executed through the agreement between the state and the local community that inhabit inside or around the forest area over the management, protection and utilization of forests owned by the state on the basis of predefined responsibilities and benefit sharing mechanisms .

10/ “Concession” means a contract given to a person with legal standing to develop, conserve or to utilize a given State forest for a defined period of time;

11/ "Protected forest" means a forest that provides various ecosystem services and is utilized in accordance with a forest management plan developed by the responsible body without

እንዲውል የተለየ ደን ነው፤

፲፪/ “ፍፁም ጥብቅ ደን” ማለት ደኑን ከአደጋ ለመጠበቅ ካልሆነ በስተቀር ከማንኛውም የሰውና የቤት እንስሳት ጣልቃ ገብነት የተጠበቀ ደን ሲሆን ለብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ለታሪካዊና ለምርምር የተለየ ደን ነው፤

፲፫/ “ምርት ሰጪ ደን” ማለት በዋናነት ለኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የለማ ደን ነው፤

፲፬/ “ሰው ሰራሽ ደን” ማለት በሰው አማካኝነት የለማ ደን ነው፤

፲፭/ “የተፈጥሮ ደን” ማለት በአብዛኛው በተፈጥሮ የበቀሉ ዛፎች፣ ቁጥቋጦና ሌሎች የእንጨትነት ባህሪ ያላቸውና የሌላቸው ተክሎችና ዕፅዋቶች ያሉበት ደን ነው፤

፲፮/ “ጥምር እርሻ ደን” ማለት ሰብልንና ዛፍን ወይም የእንስሳት መኖንና ዛፍን ወይም ሶስቱንም በአንድ መሬት ላይ በተመሳሳይ ጊዜ ወይም በማፈራረቅ በቅንጅት በማልማት የሚከናወን የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ስልት በመጠቀም የሚለማ ወይም የለማ ደን ነው፤

፲፯/ “የደን አያያዝ ዕቅድ” ማለት በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ደን ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም የደን ሀብት በዝርዝር በማጥናት ለሀብቱ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም የሚወጣ ዕቅድ ነው፤

፲፰/ “የደን ውጤት” ማለት ማንኛውም ከደን የሚገኝ የእንጨትነት ባህርይ ያለውና የሌለው ምርት እንዲሁም የደን ካረበንን ጨምሮ ማንኛውንም የደን ሥርዓተ-ምህዳራዊ ግልጋሎት የሚያካትት ነው፤

፲፱/ “የደን ውጤቶች እንቅስቃሴ ፈቃድ" ማለት የደን ውጤቶችን ወደ ሀገር ለማስገባት፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለመሸጥ እና፣ ለማምረት በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለስልጣን የሚሰጥ ፍቃድ ነው፤

፳/ “የደን ኬላ" ማለት የደን ምርት ውጤቶችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የተቋቋመ ጣቢያ ነው፤

፳፩/ “የደን ውጤቶች ተቆጣጣሪ” ማለት የደን ምርቶችን እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለስልጣን የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

affecting the sustainability of the forest eco-system value.

12/ “Preserved forest" means a forest that is free from human and domestic animal intervention preserved for the purpose of conservation of biological diversity, historical and research purpose;

13/ “Production forest" means a forest that is mainly developed for economic purpose;

14 / “Plantation forest" means a forest developed by humans;

15/ “Natural forest” means a forest which is composed of naturally grown trees, shrubs and other woody and non-woody plants;

16/ “Agro-forestry” means a forest to be developed or developed through integrated land utilization methods which combine the developing of crops with trees or animal fodder with trees or all three on the same plot of land simultaneously or through shifting;

17/ "Forest management plan" means a plan developed for the development, conservation and utilization of natural or plantation forests by conducting a detailed study of the forest resources;

18/ “Forest products” means any timber and non-timber forest products including forest carbon and other forest ecosystem services;

19/ “Forest product transaction permit" means a permit issued by the Ministry or responsible regional authority for the importation, export, transportation, storage, sale and production of forest products;

20/ “Check-post” means a station established to control the transaction of forest products;

21/ “Forest product inspector” means an expert assigned by the Ministry or responsible regional authority to inspect forest products movement;

፳፪/ "ካርበን" ማለት ህይወት ባላቸው እንዲሁም በሌላቸው አካላት ውስጥ የሚገኝ ከኦክስጅን ጋር ሲዋሃድ ሙቀት የማመቅ ባህሪይ ያለው ጋዝ የሚፈጥርና በከባቢ አየር ውስጥ ያለው ተፈጥሮዊ ክምችት በሰው ሰራሽ ምክንያቶች ሲጨምር የምድር ሙቀት መጨመርን የሚያስከትል ንጥረ-ነገር ነው፤

፳፫/ "ካርበን ማከማቸት" ማለት አረንጓዴ ዕፅዋት ምግባቸውን በሚያዘጋጁበት የተፈጥሮ ሂደት ካርበንዳይ አክሳይን በመጠቀም ካርበንን ለረጅም ጊዜ በተለያዩ ክፍሎቻቸው መያዝ ነው፤

፳፬/ "የደን ካርበን ንግድ" ማለት የደን ምንጣሮና መመናመንን በመቀነስ ወይም የደን ሽፋንን በማሳደግ የካርበን ክምችትን በመጨመር ለካርበን ልቀት ቅነሳ ክፍያ የሚፈጸምበት ግብይት ሥርዓት ነው፤

፳፭/ "የደን ካርበን ልቀት" ማለት በደን ውስጥ የተከማቸ ካርበን በተለያዩ ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ወደ ከባቢ አየር መለቀቅ ነው፤

፳፮/ "አግባብ ያለው ባለስልጣን" ማለት ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በክልል መንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል መንግስት አስፈፃሚ አካል ነው፤

፳፯/ "የሮያሊቲ ክፍያ" ማለት ማንኛውም በደን ውጤት ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ምርቱን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚከፍለውና ቀጣይነት ላለው የደን ልማት አገልግሎት የሚውል ክፍያ ነው፤

፳፰/ "የደን ኤክስቴንሽን" ማለት በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ምርጥ ተሞክሮዎች እና ቴክኖሎጅዎችን በመቀመር፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት የደን አልሚው እውቀትና ክህሎት ማሳደጊያ መንገድ ነው፣

፳፱/ "የደን ስርዓተ ምህዳር አገልግሎት" ማለት ከዘላቂ የደን ልማትና ጥበቃ የሚገኝ ማንኛውም የስርዓተ ምህዳር አገልገሎት ነው፤

፴/ "ኳራንታይን" ማለት የደን ውጤት ከውጭ ወደ ሃገር ውስጥ ሲገባና ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ ሲወጣ ከተባይ፣ ከበሽታ ነጻ መሆኑንና የደን ውጤት ደረጃ መስፈርት ማሟላቱን ለማገረጋገጥ የሚከናወን የቁጥጥር ሂደት ነው፤

22/ "Carbon" means a chemical element found in living and non-living things that creates a gas with a nature of heat absorption when mixed with oxygen; that results warming upon raise of the natural concentration in the atmosphere;

23/ "Carbon storage" means the accumulation of carbon for a long period of time in the various parts of green plants during the process of photosynthesis by using carbon dioxide;

24/ "Forest carbon trade" means a carbon market system in which payment made for carbon emission reduction by reducing deforestation and forest degradation or carbon stored by increasing forest coverage;

25/ " Forest carbon emission" means release of stored forest carbon into the atmosphere due to various man made activities;

26/ " Responsible authority" means any regional governmental executive organ that is responsible to implement forest development, conservation and utilization;

27/ "Royalty fee" means a payment made by a person engaged in the business of forest products for the movement of such products from one place to another and the payment collected from the transaction shall be allocated for sustainable forest development;

28/ "Forest" means the preparation and dissemination of best practices and technologies on the development, conservation and utilization of forests to enhance the knowledge and skills of forest developers;

29/ "Forest eco-system service" means any ecosystem service generated from sustainable forest development and the protection of a forest ecosystem;

30/ "Quarantine" means a control procedure to ensure forest products that are imported and exported are free from pest, diseases and satisfy forest product standards;

፴፩/ "የጥቅም ተጋሪነት" ማለት በመንግስትና በማህበረሰቡ እንዲሁም በማህበረሰቡ አባላት መካከል ከሚያለሙት ደን የሚገኝን ማንኛውንም ጥቅም መጋራት ማለት ነው፤

፴፪/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፫/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአካባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፴፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከቱት ክልሎችን እና የአዲስ አበባና የድሬደዋ የከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፴፭/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫.የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፬.የደን ባለቤትነት

የሚከተሉት የደን ባለቤትነት ዓይነቶች ይኖራሉ፤

፩ / የግል ደን፤

፪ / የማሕበረሰብ ደን፤

፫ / የማህበራት ደን፤

፬ / የመንግሥት ደን፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ግል ደን

### ፭.የግል ደን አልሚ መብቶች እና ማበረታቻዎች

፩/ የግል ደን አልሚ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤

ሀ) ለደን ልማት የሚውል መሬት የማግኘትና ባለው የግል የመሬት ይዞታ ላይ ደን የማልማት፤

ለ) ላለማውና ለሚያለማው ደን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የማግኘት፤

ሐ) በደን ልማት የሚያገኛቸውን የደን ውጤቶች የመጠቀም፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ገበያ የመሸጥ፤

31/ "Benefit sharing" means the allocation of benefits between government and community and among community from forests which have been collectedly developed;

32/ "Person" means any natural person or juridical body

33/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Environment, Forest and Climate Change, respectively;

34 / "Regional Sate" means any region stipulated in Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

35/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3.Scope of Application

This Proclamation shall be applicable nationwide.

## 4.Forest Ownership

There shall be the following types of forest ownership፡

1/ Private forest or;

2/ Community forest or

3/ Association forest

4/ State forest.

## SECTION TWO

## PRIVATE FOREST

### 5. Rights and Incentives of Private Forest Developer

1/ A private forest developer shall have the following rights:

a) Acquire land that has been identified for forest development and to develop that forest.

b) Obtain a certificate of title deed for developing forests in the identified forest land;

c) Utilize or sell to local and foreign markets forest products obtained from their forest development;

መ) በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀምና ንግድ ላይ ከመንግሥት ሙያዊ ድጋፍ የማግኘት፤

ሠ) የይዞታ መብቱን የማስተላለፍ፤

ረ) ከሚያለማውና በይዞታው ሥር ከሚገኝ ደን ካርበን ሽያጭና ከሥነ-ምህዳራዊ ግልጋሎቶች ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ የመሆን፤

ሰ) በሕዝብ ጥቅም ምክንያት ይዞታውን እንዲለቅ ሲደረግ ካሳ የማግኘት

ሸ) በደን ልማቱ በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ወይም በማምረት እና አገልግሎት በመስጠት ላይ እንዲሁም የደን ውጤቶች ላይ እሴት በመጨመር ወይም ባሉበት ሁኔታ የንግድ ስራ ላይ የመሰማራት፤

፪/ ለግል ደን አልሚ የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፤

ሀ) ከመሬት ሊዝ ክፍያ ነፃ የመሆንና የመጀመሪያውን አንድ የምርት ዘመን ከማንኛውም ግብር ነፃ የመሆን፤

ለ) አግባብ ያለውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ የብድር አገልግሎት የማግኘት፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ (፪) ሀ እና ለ ለተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፮. የግል ደን አልሚ ግዴታዎች

የግል ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

፩/ ደኑን ከቃጠሎ፣ ከተባይ፣ ከበሽታ እና ከወራሪ ዝርያዎች እንዲሁም ከሌሎች ጉዳቶች የመጠበቅ እና የመከላከል፤

፪/ ባለማው ደን ውስጥ ቃጠሎ፣ ተባይ፣ ወራሪ ዝርያ ወይም በሽታ ሲከሰት አግባብ ላለው አካል በአፋጣኝ ሪፖርት የማድረግ፤

፫/ በደኑ ውስጥ ያልተፈቀዱ ወይም ያልታወቁ ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለሥነ-ምህዳር ጎጂ የሆኑ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ ደቂቅ አካላትን ወይም ነፍሳትን ያለማስገባት ወይም ያለማራባት፤

፬/ የአካባቢ ደህንነትን፣ የተፋሰስና የብዝሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም በተመለከተ የወጡ ሕጎችን

d) Get professional support from federal and regional government on forest development, conservation, utilization and trade;

e) Transfer his possession rights;

f) Benefit from carbon sales and eco-system services generated from the forest he develops or which is under his possession

g) Get compensation in case of expropriation of his possession for public interest;

h) Generate forest products or provide services and conduct business by providing services as well as by adding value to the forest products.

2/ A private forest developer shall be provided with the following incentives:

a) Be free from land lease and any kind of tax for the first year of production ;

b) Access to loan upon fulfilling appropriate requirements.

c) The forest development incentives indicated under sub-article (a) and (b) of this Article shall be determined by regulation.

## 6. Obligations of Private Forest Developer

A private forest developer shall have the following obligations:

1/ Keep and protect the forest from fire, pests, disease, and invasive species as well as other damages;

2/ Urgently report the occurrence of fire, pest, invasive species and disease to the responsible body;

3/ Refrain from introducing and reproducing plants, animals and micro organizms and insects that might cause harm to humans, animals and the eco-system;

4/ Observe the laws issued in respect of environmental safety, water shade and bio-diversity conservation, development and

የማክበር፤

፭/ የአካባቢውን ጠቃሚ ባሕል፣ ልማድ እና ዕውቀት የማክበር፤

፮/ አግባብ ላለው አካል ደኑን በተመለከተ መረጃ የመስጠት፤

፯/ ለደን ልማት የተረከበውን መሬት ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ የማዋል፤

፰/ በደን ካርበን ሽያጭና በደን ሥርዓተ-ምህዳራዊ ግልጋሎቶች ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ ለመሆን የግብይት ሥርዓቱ የሚፈልገውን መስፈርት የማሟላትና የማክበር፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለማሕበረሰብ ደን

### ፯.የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች መብቶችና ማበረታቻዎች

፩/ የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፡-

ሀ) በአሳታፊ የደን አስተዳደር በፈቃደኝነት የመታቀፍ እና መንግስት የደን መሬት ብሎ በሚሰይመው ሥፍራ ወይም በወል ይዞታቸው ላይ የማህበረሰብ ደን ለማልማት ድጋፍ የማግኘት፤

ለ) ለሚያለሟቸው ደኖች የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የማግኘት፤

ሐ) በአካባቢያቸው በሚገኘው የተፈጥሮ ደን ላይ የደኖቹን ዘላቂነትና ህልውና በማይጎዳ መልኩ የመጠቀም፤

መ) መንግስት በኮንሴሽን በሚሰጠው ደን ተጠቃሚ ለመሆን እንደ ሁኔታው ቅድሚያ የማግኘት፤

ሠ) በሚያመነጩት ገቢ መደገፈ እስኪችሉ ድረስ ከመንግስት የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የግብዓት ድጋፍ እና የሕግ አገልግሎት የማግኘት፤

ረ) በሚያዘጋጁት የአያያዝ ዕቅድ መሠረት የደን ውጤቶችን የመጠቀም፤ የማንቀሳቀስ እና እሴት የመጨመር፤

ሰ) አባላቱ በጋራ በሚያዘጋጁት ውስጠ ደንብ መሠረት ከሚያለሙት ደን ከሚገኝ ማንኛውም ጥቅም የመጋራት፤

utilization;

5/ Respect the important local culture, custom and knowledge;

6/ Provide the relevant authority with information about the forest;

7/ Use the acquired forest land only for the intended purpose;

8/ Fulfill and respect the required criteria of the transaction system in order to benefit from carbon and ecosystem services sales income.

## SECTION THREE
## COMMUNITY FOREST

### 7. Rights and Incentives of Community Forest Developers

1/ Community forest developers shall have the following rights:

a) Voluntarily engage in participatory forest management and get support to develop a forest on their communal land or areas designated by the government as forest land;

b) Obtain a certificate of title deed for the forests they are developing;

c) Share benefits generated from the natural forests surrounding them without affecting their sustainable existence;

d) Get priority, as appropriate, to benefit from the forests concession given by the government;

e) Get professional, technical, inputs support and legal services until they are able to rely on their self-generated income;

f) Utilize, transact and add value on forest products in accordance with their management plan;

g) Share any benefits generated from the forest development as per the community by-laws;

ሸ) በሕዝብ ጥቅም ምክንያት የደን ይዞታቸውን እንዲለቁ ሲደረጉ ካሣ የማግኘት፡፡

፪/ለማሕበረሰብ ደን አልሚዎች የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፦

ሀ)ለመጀመሪያ ሁለት የምርት ዓመታት ከማንኛውም የደን ልማት ገቢ ግብር ነፃ የመሆን፤

ለ) አግባብ ያለውን መስፈርት አሟልተው ሲገኙ የብድር አገልግሎት የማግኘት፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሀ እና ለ ለተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፰.የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች ግዴታዎች**

የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፦

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱ ግዴታዎች በማሕበረሰብ ደን አልሚዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፪/ የደን አያያዝ ዕቅድ እና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አግባብነት ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት ዘንድ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

**ክፍል አራት**

**ማህበራት ደን**

**፱. የማህበራት ደን አልሚዎች መብቶች**

፩/ የማህበራት ደን አልሚዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

ሀ) በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሱት መብቶች ለማህብራት ደን አልሚዎችም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

ለ) አግባብ ባለው የመንግስት አካል የመመዝገብ፤

፪/ የማህበራት ደን አልሚዎች የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይኖሩታል፦

ሀ) ለመጀመሪያው አንድ የምርት ዘመን ከማንኛውም ግብር ነፃ የመሆን፤

h) Get compensation in case of expropriation of possession for public interest;

2/ Community forest developer shall be provided with the following incentives:

a) Exemption from any forest development income tax for the first two consecutive production years;

b) Access loan upon fulfilling appropriate requirements.

c) The forest development incentives indicated under sub-article (a) and (b) of this Article shall be determined by regulation.

**8. Obligations of Community Forest Developers**

Community forest developers shall have the following obligations:

1/ the obligations provided under Article 6 of this Proclamation shall also be applicable to community forest developers;

2/ keep at the office of the responsible government organ the forest management plan and community by laws.

**SECTION FOUR**

**ASSOCIATION FOREST**

**9. Rights of Associations of Forest Developers**

1/ Associations of forest developers will have the following rights

a) All rights and incentives indicated in Article 5(1) concerning private forest developers are also valid for associations of forest developers;

b) Register with the appropriate government body

2/ Associations of forest developers shall be provided with the following incentives:

a) Be free from any kind of tax for the first productionyear;

ለ) አግባብ ያለውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ የብድር አገልግሎት የማግኘት፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ፪ ሀ እና ለ ለተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፲. <u>የማህበራት ደን አልሚ ግደታዎች</u>**

፩/የማህበራት ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎችን ይኖሩታል፤-

ሀ) በዚህ አዋጅ በክፍል ሁለት አንቀጽ ፮ የተጠቀሱት የግል ደን አልሚዎች ግዴታዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሙሉ በማህበራት ደን አልሚዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፤

ለ) አባላትን በማስተማርና በማስልጠን በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያላቸውን እውቀትና ክህሎት በማዳበር ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህልን የማጎልበት ሃላፊነት ይኖባቸዋል፤

ሐ) ማህበሩ ከሁለት የምርት ዘመን በኋላ የገቢ ግብር የመክፈል፤

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>ስለመንግስት ደን</u>**

**፲፩. <u>የመንግስት ደን</u>**

የመንግስት ደን እንደሚከተለው ይከፈላል፤-

፩/ ምርት ሰጪ ደን

፩/ ጥብቅ ደን

፫/ ፍጹም ጥብቅ ደን

**፲፪. <u>ምርት ሰጪ የመንግሥት ደን</u>**

ምርት ሰጪ የመንግስት ደንን በተመለከተ መንግስት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

፩/ ደኑ የራሱ አስተዳደርና አመራር እንዲኖረው በማድረግ፣ በተገቢው በጀት፣ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ እንዲሟሉ ያደርጋል፤

፪/ ደኑ በአግባቡ እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና በጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፫/ የአካባቢው ህብረተሰብ በመንግስት ምርት ሰጪ ደኖች ልማትና ጥበቃ ላይ እንዲሳተፉ፣ የልማቱም

b) Access to a loan upon fulfilling the appropriate requirements.

c) The forest development incentives indicated under sub-article (a) and (b) of this Article shall be determined by regulation.

**10.<u>Obligations of Associations of Forest Developers</u>**

Associations of forest developers will have the following obligations:

a) All obligations indicated under Article 6 also apply to Associations of forest developers.

b) Educate and train their members to improve their knowledge and skill on forest development, protection and utilization in order to develop members' social and economic responsibilities,

c) The association shall pay income tax after two harvest periods.

**<u>SECTION FIVE</u>**

**<u>ABOUT STATE FOREST</u>**

**11. <u>State Forest</u>**

State forest shall be classified as follows:

1/ productive forest

2/ protected forest

3/ preserved forest.

**12. <u>Productive State Forest</u>**

Government shall have the following responsibilites with respect to the productive state forest:

1/ Put in place administrative and management system for the forest and allocate the necessary budget, manpower and material;

2/ Cause the proper development, conservation and utilization of the forest;

3/ Formulate forest development, conservation and utilization plans to allow the participation of local communities in the development and conservation and also in the sharing

ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መርሐ-ግብር ይቀይሳል፤

፬/ ደኑን የወራሪነት ባህሪይ ካላቸው አረሞች፣ ከተባይ እና ከበሽታ ይከላከላል፤ ሲከሰትም በቁጥጥር ሥር እንዲውል ያደርጋል፤

፭/ የደን ሀብቱ ከተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎችና ጥፋቶች እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

፮/ ለደኑ ልማት የሚያገለግሉ መንገዶችና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን ይሰራል፤

፯/ ከደኑ የሚገኘውን ዘላቂ ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል የደን አስተዳደር ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ይጠብቃል፤ ያስተዳድራል፤

፰/ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በፌደራልና በክልል አካላት ዘንድ የተጠናከረ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤

፱/ በተለዩ የደን መሬቶች ላይ አዳዲስ ምርት ሰጪ ደኖች እንዲለሙ ያደርጋል፤

፲/ ደኖቹ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

፲፫. **<u>ጥብቅ ደኖች</u>**

መንግስት ጥብቅ ደኖችን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

፩/ አሳታፊ የደን አያያዝ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪/ በጥብቅ ደንነት የተሰየሙና ዕፅዋት የማይገኝባቸው ወይም በበቂ ደረጃ በእፅዋት ያልተሸፈኑ የደን መሬቶች በሚወጣላቸው የልማት ዕቅድ መሠረት እንክብካቤና ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ደን እንዲለማባቸው ያደርጋል፤

፫/ በደኖች ዙሪያ የደኑን ዳር ድንበር የሚያመለክቱና ለአካባቢው ሕብረተሰብ ለማገዶና ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ፈጣን ዕድገት ያላቸው የዛፍ ዝርያዎች እንዲለሙ ያደርጋል፤

፬/ ደኖቹ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

of benefits from the forest;

4/ Protect the forest from invasive species, pests and diseases; and apply curative measures in case of occurrence of same;

5/ Protect the forest resources from natural and man-made disasters;

6/ Build roads and other f acilities for the development of the forests;

7/ Conserve and administer the forest by developing a forest management plan to ensure the sustainability of forest benefits;

8/ Establish strong and integrated working relationships among the federal and regional bodies in order to develop, conserve and utilize the forest sustainably and efficiently;

9/ Develop new productive forests on designated forest lands;

10/ Cause issuance of a certificate of title deed which is supported with maps;

13. **<u>Protected Forest</u>**

Government shall have the following responsibilities in relation to protected forests

1/ Prepare and implement participatory forest management plan for forests;

2/ Rehabilitate and protect or develop plans as per the approved development plans on forest lands designated as protected forests and which are without or with less plant coverage;

3/ Establish fast-growing tree species plantation along the periphery of the forests to indicate demarcation of the forest and to be used by the local community for firewood and construction;

እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

**፲፬. <u>ፍፁም ጥብቅ ደኖች</u>**

መንግስት ፍጹም ጥብቅ ደኖችን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

፩/ ደኖቹ ወሰናቸው ታውቆ ተከልለው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፪/ ለምርምር፣ ለትምህርት እና ከማንኛውም ውድመትና ጥፋት ለመጠበቅ ከሚወሰዱ ተግባራት ውጭ ከማንኛውም ዓይነት የሰውም ሆነ የቤት እንስሳት ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፫/ ደኖቹ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

**፲፭. <u>የመንግሥት ምርት ሰጪ ወይም ጥብቅ ደን አስተዳደር እና አጠቃቀም</u>**

፩/ ደኑ በጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው በተዘጋጀውና ኃላፊነት ባለው አካል በፀደቀ የደን የአያያዝ ዕቅድ መሰረት መሆን አለበት፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ደኑ ጥቅም ላይ የሚውለው በመንግሥታዊ ድርጅቶች ወይም ደኑ በኮንሴሽን በተሰጣቸው አካላት ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፣

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) እንደተጠበቁ ሆነው ደኑ አስቀድሞ በተዘጋጀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት በደኑ ዙሪያ ወይም በደኑ ውስጥ የሚኖሩ የህብረተሰብ አባላት አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን እንደየአካባቢው ሁኔታ አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲፈቀድ ሊያገኙ ይችላሉ፤

፬/ የደኑ አስተዳደር ሥርዓት ከኤኮ-ቱሪዝም፣ ከካርበን ንግድ እና ሌሎች ተጓዳኝ የሥርዓተ-ምህዳር ግልጋሎቶች ገቢ እንዲያስገኝ መደረግ ይኖርበታል፣

4/ Cause issuance of a certificate of title deed which is supported with maps.

**14. <u>Preserved Forests</u>**

Government shall have the following responsibility in relation to preserved forests:

1/ Demarcate and protect the forests;

2/ Ensure their protection from any human and domestic animals intervention except for the purpose of research, education, and disaster prevention;

3/ Cause issuance of certificate of title deed which is supported with maps.

**15. <u>Management and Utilization of Productive State or protected Forest</u>**

1/ The forest shall be utilized in accordance with the management plan prepared and approved by responsible authority.

2/ The utilization of forests in accordance with sub- article (1) of this Article shall be undertaken by government organizations or persons who are given concessions. The details shall be determined by regulation.

3/ Without prejudice to sub-article of (1) and (2) of this Article, the local community that resides inside or at the periphery of the forest may obtain the environmental, social and economic benefits depending on the local situation in line with the forest management plan upon obtaining permit from the responsible authority.

4/ The management of the forest shall be in a manner to generate revenues from eco-tourism, carbon trade and other related eco-system services;

## ክፍል ስድስት
## የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### ፲፮.የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ፤-

፩/ ይህን አዋጅ ከሚመለከታቸው የክልል ተቋማት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፪/ የደረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት የሀገሪቱን ደን መረጃ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፤

፫/ የደን አልሚዎች ዕውቀትና ክህሎት እንዲያድግ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬/ ጥቃቅንና አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የደን ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤

፭/ የደን ውጤት ደረጃዎች እንዲወጣ ያደርጋል፤

፮/ ዘላቂ እና ዘመናዊ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት ለክልሎች የቴክኒክና የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋል፤

፯/ በደን ውጤቶች ላይ የጥቅም ተካፋይነትን ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፰/ በደን ሀብት ላይ አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የመከላከያ እና የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያዘጋጃል፤ ሲከሰቱም ክልሎችንና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤

፱/ የኳራንታይን ሥርዓት ያዘጋጃል፤ መተግበሩንም ይቆጣጠራል፤

፲/ የደን ሙያ፣ የደን ልማትና የደን ውጤቶች ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ይሰጣል፤

፲፩/ በህብረተሰብ ተሳትፎ ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የደን ልማት ስራን ባለቤት እንዲኖራቸው ይከታተላል፣ ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፪/ የደን ምርምር እና የስልጠና ተቋማትን በማቋቋም ሀገር በቀል ዕውቀቶች እንዲያድጉ ያደርጋል።

## SECTION SIX
## POWER AND DUTIES OF EXECUTIVE ORGANS

### 16. Power and Duties of the Ministry

The Ministry shall:

1/ Ensure the implementation of this Proclamation in collaboration with the responsible regional sector;

2/ Ensure users' access to information about the forest of the countries by establishing an information communication system;

3/ Provide professional support to enhance the knowledge and skills of forest developers;

4/ Provide support to the micro and small, medium and large-scale forest industries to increase their number and to make them competitive;

5/ Initiate the development of forest product standards;

6/ Provide technical and material support to the regions to establish a sustainable and modern forest development, conservation and utilization system;

7/ Develop a system in order to determine benefit sharing right of forest products;

8/ Develop an early warning, prevention and control mechanism to prevent the occurrence of damage to forest resources and, upon the occurrence of damage, to take emergency measures by coordinating regional and other relevant bodies;

9/ Develop and control the implementation of a quarantine system;

10/ Issue forest professional, forest development and forest product trade competence certificates;

11/ Follow up watershed based forest development to have owners, and also provide technical support;

12/ Establish forest research and training centers to enhance indigenous knowledge and practices to promote forest development.

፲፫/ እያንዳንዱ ክልል በክልሉ ውስጥ የሚገኝን ማንኛውንም የመንግሥት ደን በዚህ አዋጅ መሠረት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ቢሆንም፦

ሀ) ደኑ በሚገኝባቸው አጎራባች ክልሎች በጋራ በአግባቡ ሊለማና ሊጠበቅ የማይችል ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) ደኑ ወይም የደን መሬቱ ከሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ጠቀሜታው አንፃር በፌደራል መንግስት ሥር ሆኖ መተዳደር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤የፌደራል መንግስት ሊያስተዳድር ይችላል፡፡

**፲፯. <u>የክልል አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የክልል አስፈጻሚ አካል፤-

፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፮ ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም የደን መሬት እና የመንግስት ደን ያስተዳድራል፤ የግል፣ የማህበራት እና የማህበረሰብ ደኖች በዚህ አዋጅ መሠረት መልማታቸውን፣ መጠበቃቸውን እና መተዳደራቸውን ይቆጣጠራል ይደግፋል፤

፪/ ደን እና የደን መሬቶችን ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፫/ ህብረተሰቡን ያሳተፈ የደን ልማት ፕሮግራም እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬/ ለደን ልማት በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ደን አልሚ መሬቱን ለደን ልማት ዓላማ ማዋሉንና በሚያዘጋጀው የደን አያያዝ እቅድ መሠረት መተግበሩን በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤

፭/ የደን ውጤቶች ሮያሊቲ ክፍያ ተመን ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ ያስወስናል ይሰበስባል፤

፮/ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት ይፈጥራል፤ በጀት ይመድባል፣ የሰው ሀይል ያሟላል፤

13/ Notwithstanding the power of each regional state to administer its forest resource in accordance with this Proclamation, the Federal Government may take over and administer, in cases where:

a) The forest could not be properly developed and conserved jointly by neighboring regional states;

b) It becomes necessary to administer the forest or forest land by the federal government because of its national, regional and international significance.

**17. <u>Duties and Responsibilities of the Regional Executive Organs</u>**

Executive organs of the Regional States:

1/ Without prejudice to Article 16 of this Proclamation, shall administer any forest land and state forest found in the regional state; supervise and support the development, conservation and administration of private and community forests in line with this Proclamation;

2/ Cause provision of legal recognition for the forests and forest lands;

3/ Encourage forest development programs, which involve the participation of community and provide technical support;

4/ Regularly monitor and evaluate whether forest developers given land on which to develop forests have used the land for the intended purpose and whether the use of the land is in accordance with the agreed forest management plan;

5/ Set and collect rates of royalty payment for forest products;

6/ Shall establish or provide the institutional arrangements, budget allocation and manpower required for the implementation of this Proclamation;

፯/ በደን ሀብት ላይ አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የመከላከያ እና የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያዘጋጃል፤ አደጋ ሲከሰትም ህብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ እንደስፈላጊነቱ የሚኒስቴሩን ድጋፍ ይጠይቃል፤

፰/ በህብረተሰብ ተሳትፎ ተፋሰስን መሰረት ያደረጉ የደን ልማት ስራዎችን ባለቤት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሰባት
## የደን ኤክስቴንሽንና ገበያ ማስፋፋት

### ፲፰.የደን ኤክስቴንሽን

መንግስት፣

፩/ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ምርጥ ተሞክሮዎች እና ቴክኖሎጅዎችን በመቀመር፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት የደን አልሚው እውቀትና ክህሎት እንዲያድግ፣

፪/ የደን ልማት ግብአት አቅርቦት ሥርዓት እንዲዘረጋ፣

፫/ በደን ልማት ለተሰማሩ ሰዎች ዘመናዊ የደን ልማት፣ አያያዝ፣ ቴክኖሎጂ እና የገበያ እውቀት እንዲኖራቸው ሥልጠና እንዲያገኙ፣

፬/ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የኤክስቴንሽን ፓኬጅ በማዘጋጀት እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

### ፲፱.የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም

፩/ መንግስት የመንግስት የደን ሀብት በጥብቅ፣ ፍፁም ጥብቅና በምርት ሰጪ ደንነት ተለይተው እንዲመዘገቡ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፪/ መንግስት ለካርበን ንግድ የሚሆን የደን መሬት ወይም ደን ሊከልል ይችላል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚፈጸሙ ደን የመለየትና የመከለል ተግባራትን የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ የሚከናወኑ ይሆናል፤

7/ Develop an early warning, prevention and control mechanism to prevent the occurrence of damage to forest resources and upon the occurrence of damage take emergency measures by mobilizing the community and other relevant stakeholders; and request the Ministry for support if deemed necessary;

8/ Provide ownership for forest development based on watershed through community participation;

## SECTION SEVEN
## FOREST EXTENSION AND MARKET PROMOTION

### 18.Forest Extension

Government shall:

1/ Prepare and disseminate best practices and technologies on the development, conservation and utilization of forests to enhance the knowledge and skills of forest developers;

2/ Establish a system for the supply of forest development input;

3/ Provide training on forest development, management, technology and market skills for those who are engaged in forest development;

4/ Prepare and implement forest development, conservation and utilization extension package.

### 19.Forest Development, Conservation and Utilization

1/ In order to develop, conserve and utilize the state forest, the government has to identify and register the state forest as either a productive, protected and preserved forests.

2/ The government may demarcate a forest or forest land for the purpose of carbon trade.

3/ The identification and demarcation of a forest pursuant to sub-article, (1) and (2) of this Article shall be conducted though participation of the local community.

፬/ በዚህ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የተለየና የተከለለ የመንግሥት ደን ደኑ በሚገኝበት ክልል መንግሥት ዕውቅና ያገኛል፤

፭/ መንግስት የአካባቢው ሕብረተሰብ በመንግሥት ደኖች ልማትና ጥበቃ ላይ እንዲሳተፉ፣ የልማቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መርሐ-ግብር ይቀይሳል፤

፮/ መንግስት በደን ልማት ዘርፍ ኢንቨስት በማድረግ በልማቱ ይሳተፋል፤

፯/ መንግስት በይዞታው ስር ካሉ ደኖች በኮንሴሽን ሊለሙ የሚችሉ የደን ቦታዎችን በመለየት በኮንሴሽን ውል እንዲለሙ ሊያደርግ ይችላል፤

፰/ መንግሥት በጥብቅ ወይም በምርት ሰጪ ደንነት የተከለሉ ደኖችን የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ግለሰቦች፣ ማህበራት ወይም ባለሀብቶች በሚመለከተው አካል በሚወጣ መመሪያ መሠረት የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማሳተፍ የአያያዝ ዕቅድ አዘጋጅተው፤ ጠብቀውና አልምተው እንዲጠቀሙ ያደረጋል፤

፱/ መንግስት በደኑ መኖር ተጠቃሚ የሆኑ አካላትን ለደን ልማትና ጥበቃ አስተዋፅኦ እንድያደርጉ ስርዓት ይዘረጋል፤

፲/ መንግስት የጥምር እርሻ ደን ዘዴ በይበልጥ በአርሶ አደሩ፣ በከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደር ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የዕፅዋት ዘርና ችግኝ በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ያደረጋል፤

፲፩/ መንግስት በደን እና የደን መሬት ውስጥ የሰፈሩ ሰዎች ለልማቱ እንቅፋት በማይሆኑበት መንገድ ኑሮአቸውን የሚመሩበትና በልማቱና በጥበቃው ተግባር እንዲሳተፉ በማድረግ ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ ወይም በጥናት ላይ በመመስረት ከደኑና ከደን መሬቱ ውስጥ ወጥተው ሕይወታቸውን ሊመሩ በሚችሉባቸው ስፍራዎች እንዲሰፍሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመወያየት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ያደረጋል፤

4/ The forest identified and demarcated pursuant to sub-article (1) and (2) of this article shall obtain the recognition of the regional state.

5/ Government shall formulate forest development, conservation and utilization plans to allow the participation of the local community in the development and conservation and also in the sharing of benefits from the development of state forests.

6/ The government, through investing in the forest sector, shall participate in its development.

7/ Government may identify forests under its possession and given through concession agreement for forest development.

8/ Forests that are designated as protected or productive state forests may be given to the community, associations or investors so that they conserve and utilize them in accordance with forest management plan and a directive that issued by the responsible body.

9/ The government shall develop a system to ensure that those who benefit from the forest contribute to the development and conservation of forests.

10/ The Government, in order to introduce agro-forestry practices among the farming, semi-pastoral and pastoral communities, shall provide them with sufficient amount of plant seeds and seedlings of tree species that could have different economic benefits.

11/ Government shall facilitate conditions whereby inhabitants within state forests and state forest land shall continue living in the forest, while participating in the development and conservation of the forest, in manner that shall not obstruct forest development; or based on a study and in consultation with the appropriate body, they shall evacuate the forest area and settle in other areas suitable for living.

፲፪/ መንግስት የግልና የማህበረሰብ ደን ልማትን ለማስፋፋት ለደን ልማትና የደን ውጤቶች ማምረቻ የሚውሉ መሣሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች እንደአስፈላጊነቱ ከታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት እና ሌሎች የድጋፍና የማበረታቻ ሥርዓቶች ያዘጋጃል፣

፲፫/ መንግስት የከተማ ደን ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

**፳.** **<u>የደን ውጤቶች ገበያ ማስፋፋት</u>**

መንግስት፣-

፩/ ደን አልሚዎች ጥራቱን የጠበቀና ለገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የደን ውጤቶችን በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

፪/ በደን የአያያዝ ዕቅድ መሠረት የደን ውጤቶች ለንግድና ለኢንዱስትሪ ልማት እንዲውሉ እገዛ ያደርጋል፣

፫/ ለደን ውጤቶች ንግድ የሚሰጠው ፈቃድ የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት ዘለቄታዊ አጠቃቀም ባገናዘበና የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት መዛባት በማያስከትል መንገድ በሚዘጋጅ የአያያዝ ዕቅድ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

፬/ በገበያ ተፈላጊ ለሆኑ የዛፍ ዝርያዎች ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣

፭/ በደን ልማት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰዎች በደን ውጤቶች ግብይት ላይ ተከታታይ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፮/ የደን አልሚዎችን በደን ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለማሳተፍ የሚያስችሉ ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ማበረታቻዎች እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፯/ የደን ውጤቶች ገበያ መረጃ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለደን አልሚና ተጠቃሚ ህብረተሰብ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

12/ For promoting the private and community forest development, government shall support, as may be necessary, provide incentives and tax exemption on imported tools and technologies used for forest products production and forest development;

13/ The government shall ensure the enhancement of urban forests.

**20. <u>Expansion of the Forest Products Market</u>**

Government shall:

1/ Provide the necessary support to forest developers to enable them to produce and supply quality and competitive forest products for the local and foreign markets;

2/ Provide assistance to use forest products as an input for trade and industry development as per the forest management plan;

3/ Ensure that a license issued for forest product trade is in accordance with the relevant management plan and takes into account the utilization of the country's limited forest resources and applies in a manner that shall not disturb the natural resource balance of the area;

4/ Establish a system for the conservation of tree species, having market demand, with a view to increase their sustainable product and productivity;

5/ Provide a continuous training to the persons engaged in forest development on the marketing of forest products;

6/ Create favorable investment opportunities and incentives to investors engaging in the forest industry;

7/ Disseminate forest products market information to forest developers and forest product consumers through various mass media.

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፩.የደን አደጋዎችን መከላከል**

፩/ አግባብነት ያላቸው የመንግስት አካላት የደን ቃጠሎን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ተከታታይ ሥልጠና የመስጠትና የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ በደን ውስጥ ወይም በአካባቢው የሚኖር፣ የሚሰራ ወይም የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው የደን ቃጠሎ እንዳይነሳ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ የደን ቃጠሎ መነሳቱን የተረዳ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የመንግሥት አካልና ማኅበረሰብ ወይም ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ የደን ቃጠሎ ሲነሳ በየደረጃው ያለው የአስተዳደር አካላት፣ መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማትን እንዲሁም የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማስተባበርና በማንቀሳቀስ እሳቱን ለማጥፋት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡

፭/ በአካባቢው የሚገኙ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋሞች እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ አባላት የተነሳውን የደን ቃጠሎ ለማጥፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ የመሣተፍ ግዴታ አለባቸው፡፡

፮/ ከክልል አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ የደን ቃጠሎ አደጋ ሲከሰት ሚኒስቴሩ የማስተባበር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

፯/ የደን ባለቤቶች በይዞታቸው ሥር ባለ ደን ውስጥ ተባይና በሽታ ሲከሰት፣ ተስፋፊነት ያላቸው አረሞች ሲከሰቱ አግባብ ላለው ባለሥልጣን በአፋጣኝ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

፰/ ማንኛውም ሰው በደን ውስጥ ያልተፈቀዱ ወይም ያልታወቁ ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለሥነ-ምህዳር ጎጂ የሆኑ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን ወይም ደቂቅ አካላትና ነፍሳትን ማስገባት ወይም ማራባት አይቻልም፡፡

## PART EIGHT
## MISELLANEOUS PROVISIONS

**21.Prevention of forest Hazards**

1/ The relevant government bodies shall have the responsibility to provide a successive training to prevent the occurrence of forest fires and establish an early warning system.

2/ Any person who inhabits works or travels across or around a forest shall have the responsibility to take the necessary precautions to prevent the occurrence of forest fires.

3/ Any person who is aware of the occurrence of a forest fire shall have the duty to immediately report the same to the nearest government body and the community, or to the Ministry.

4/ The respective administrative bodies shall, in the occurrence of forest fire, have the duty to take the necessary measures by coordinating and mobilizing governmental, non-governmental and private organization operating in the locality and the local community to extinguish the fire.

5/ The governmental, non-governmental organizations and private institutions that are operating in the locality or that have specific responsibility shall have the obligation to participate in the effort to extinguish the forest fire.

6/ The Ministry shall have the responsibility to coordinate the response to the occurrence of forest fire when this is beyond the capacity of regional states.

7/ Forest owners shall report as soon as possible to the responsible authority when a forest under their possession or control encounters outbreak of pests, disease and introduction of invasive weeds.

8/ No person shall introduce and reproduce plants, animals and micro-insects that might cause harm on human being, animals and the eco-system

**፳፪.የደን ውጤቶችን ማምረትና ማንቀሳቀስ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከራሱ ይዞታ ካልሆነ በስተቀር ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ወይም ከሚመለከተው የባለይዞታ ፈቃድ ሳያገኝ ከማንኛውም ደን ውስጥ የደን ውጤቶችን ማምረትና ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በግል ካለማው የሰው ሰራሽ ደን በስተቀር የደን ውጤት ከቦታ ቦታ ከማጓጓዙ በፊት የደን ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢ አግባብ ላለው የመንግስት ባለሥልጣን በቅድሚያ በማሳወቅ የደን ውጤቶች እንቅስቃሴ ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተውን በመተላለፍ የተያዘ የደን ውጤት ሊበላሽ የሚችል ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የደን ውጤቱን በወቅቱ የገበያ ዋጋ ሸጦ ገንዘቡን በጉዳዩ ላይ የፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ አግባብ ባለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽሕፈት ቤት ዘንድ በአደራ ያስቀምጣል፡፡

**፳፫.የደን ጠባቂዎች እና የደን ውጤት ተቆጣጣሪዎች**

፩/ የመንግሥት ደን ጠባቂዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ደኖችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ የተደነገጉትን በመተላለፍ ከሚፈፀሙ ድርጊቶች የመጠበቅ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የደን ውጤት ተቆጣጣሪዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት፣

ሀ) ሕገወጥ የደን ውጤቶችን የጫነ ወይንም ለመጫኑ የሚጠረጠርን ማናቸውንም ማጓጓዣ በደን ክልል መግቢያና መውጫዎች እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በሚመረጡ የሀገር ውስጥ እና የድንበር ኬላዎች ላይ አስቁሞ የመፈተሽ፣

ለ) የደን ውጤቶችን ሲያጓጉዝ፣ ሲያዘጋጅ ወይም አከማችቶ የተገኘ ሰው የደን ውጤቶቹን መጠን፣ መነሻና መድረሻ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ወይም ማናቸውንም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርብ የመጠየቅ፣

**22.Production and Transportation of Forest Products**

1/ No person shall, otherwise from his possession, harvest forest products from any forest without having the necessary permit from the Ministry or responsible regional authority or relevant private forest owner.

2/ Any person shall, except from private development plantation forest, obtain a transaction permit from the Ministry or responsible regional authority for the transaction of all forest products from place to place.

3/ Where a forest product seized due to the violation of sub-article (1) or (2) of this Article are perishable, the Ministry or responsible regional authority shall sell the product at the current market price and keep the proceeds with relevant office of finance and economic cooperation until a court ruling is given on the case.

**23. Forest Guards and Forest Products Inspectors**

1/ Forest guards shall, in accordance with the directives given to them by the Ministry or responsible regional authority, have the power to protect against acts committed in violation Article 23 of this Proclamation.

2/ Forest products transaction inspectors shall, in accordance with directives by Ministry or responsible regional authority, have the power and duties to:

a) Inspect, at forest entry or exit points as well as inland and boarder check posts to be identified as appropriate, any means of transport carrying or suspected for carrying forest products;

b) Require any person who transports processes or store forest products to produce certificate of origin and destination or any other legal document to this effect;

ሐ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተዘጋጅተው ሲጓጓዙ ወይም ተከማችተዉ የተገኙ የደን ውጤቶችን በመያዝ የድርጊቱ ተጠያቂዎችን ወዲያውኑ ለሚመለከተው ፍትሕ አካል ማቅረብ፤

መ) ስለተያዙ የደን ውጤቶች ዝርዝር ሁኔታ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው የክልል ባለሥልጣን ሪፖርት የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው ሃላፊነት አለባቸው

፫/ የደን ጠባቂዎችና የደን ውጤቶች ዝውውር ተቆጣጣሪዎች በሥራቸው ላይ በሚሆኑበት ጊዜ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚወሰነው መሠረት የደንብ ልብስ የመልበስና መታወቂያ ወረቀት የመያዝ፣ በተጠየቁም ጊዜ ማሳየት አለባቸው፡፡

## ፳፬.የመጠቆም ግዴታና ማበረታቻ

፩/ ማንኛውም ሰው ማናቸውንም ሕገወጥ የደን ውጤቶች ዝግጅትን፣ ዝውውርን፣ ወይም ክምችትን የተመለከተ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል መጠቆም አለበት፤

፪/ ሕገ ወጥ የደን ውጤቶች በሚመለከት ጥቆማ ሚያቀርቡ ወይም ለሚይዙ ሰዎች ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ክልል ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

## ፳፭.የተከለከሉ ድርጊቶች

፩/ ማንኛውም ሰው በመጥፋት ላይ የሚገኙ በተፈጥሮ የበቀሉ ሀገር በቀል ዛፎችን ከመንግሥት ደን ውስጥ እንዲሁም በተፈጥሮ በቅለው የሚገኙና በማህበረሰብ ይዞታነት ሥር ካሉ ደኖች መቁረጥ አይችል፡፡

፪/ በተፈጥሮ የበቀሉና ለመጥፋት የተጋለጡ ሀገር በቀል ዝርያዎችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለይዞታው በባለቤትነት ራሱ ተክሎ ያለማቸውን በመጥፋት ላይ የሚገኙ የዛፍ ዝርያዎች የሚመለከተው አካል አረጋግጦ በሚሰጠው ፍቃድ መሰረት ሊጠቀም ይችላል፡፡

c) Seize, together with the culprit, forest products being transported, processed or stored in violation of the provision of this proclamation;

d) Report immediately to the Ministry or the responsible regional authority on the details of the forest products seized.

3/ Forest guards and inspectors of forest products transaction shall, while on duty, have the obligation to wear uniform and carrying identification cards and show the same upon request.

## 24. Obligation to Notify and Incentives

1/ Any person shall have the obligation to notify, any illegal transportation, processing or possession of forest products to responsible authority.

2/ Informants and persons who seize illegal forest products may be rewarded in accordance with directives to be issued by the Ministry or the responsible regional body

## 25.Prohibited Activities

1/ No person shall be allowed to cut endangered indigenous naturally grown trees from state forest or those naturally grown in the community forest.

2/ The list of endangered indigenous natural tree shall be determined by directives issued by the Ministry.

3/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article the owner of the tree may utilize endangered tree species planted in his possession upon confirmation from the responsible authority.

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩ እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ወይም ከባለ ይዞታው የጽሁፍ ፈቃድ ካልተሰጠው ወይም በራሱ ይዞታ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከማንኛውም ደን ውስጥ፣

ሀ) ዛፍ መቁረጥ፣

ለ) በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት መስፈር፣

ሐ) የቤት እንስሳትን ለግጦሽ ማሰማራት፣

መ) አደን ማካሄድ፣

ሠ) የእንጨት መሰንጠቂያ መጋዞችና ሌሎች ለደን ጭፍጨፋ የሚረዱ መሣሪያዎች ይዞ መገኘት፣

ረ) ቀፎ መስቀል ወይም ማር መቁረጥ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን መፈጸም አይችልም፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በደን የተሸፈነወይም የደን መሬት ለልማት ፕሮጀክቶች እንዲሰጥ ሲወሰን የአካባቢና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ቀርቦ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፡

## ፳፮.<u>ቅጣት</u>

፩/ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመንግሥት፤ ከማህበረሰብ እና ከግል ደኖችና የደን መሬቶች ዛፎችን ከባለ ይዞታው ፈቃድ ውጭ የቆረጠ ወይም የደን ውጤቶችን የወሰደ ፤ለዚህ ተግባር የተባበረ ወይም በማንኛውም በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ የደን ውጤት ይዞ የተገኘ ወይም የተጠቀመ ማንኛውም ሰው የደን ውጤቱ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ፲(አስር ሺ) ብር እስከ ፳(ሀያ)ሺ.ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ የደን የወሰን ምልክቶችን ያጠፋ፣ ያበላሸ ወይም ያዛባ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ ፲(አስር)ሺ.ብር እስከ ፴ (ሰላሳ) ሺ.ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡

4/ Without prejudice to sub-article (1) and (2) of this Article, unless in possession of written permit from the Ministry or relevant regional authority or owner of the forest, or he is the owner, no person shall, with in a state forest:

a) cut trees;

b) settle permanently or temporarily;

c) graze domestic animals;

d) undertake hunting activities;

e) carry cutting saws and any other tree cutting tools;

f) keep bee-hives or extract honey or other similar activities.

5/ Without prejudice to sub-article (4) of this Article any development projects to be carried out in areas covered with forest or demarcated as forest land shall pass through environmental and social impact assessment that has to be approved by Ministry or appropriate regional authority.

## 26.<u>Penalty</u>

1/ Any person who, except pursuant to this Proclamation and directives issued here in under, cuts trees or removes, process, or uses in any way forest products from state, community, and private forest without the permit of the forest possessor shall, without prejudice to confiscation of the forest product, be punishable with rigorous imprisonment not less than one year and not exceeding five years and with fine from Birr 10,000 to Birr 20,000.

2/ Any person who destroys damages or falsify forest boundary marks shall be punishable with rigorous imprisonment not less than one year and not exceeding three years and with fine from Birr 10,000 to Birr 30,000.

፫/ ሆነ ብሎ እሳት በመለኮስ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በደን ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከ፲ (አስር)ዓመት በማያንስና ከ፲፭(አስራ አምስት) ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤ ጉዳቱ የደረሰው በቸልተኝነት ከሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ፭(አምስት)ሺ ብር እስከ ፲(አስር)ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬/ ደን እና የደን መሬት ተብሎ በተከለለ ስፍራ የሰፈረ ወይም የእርሻ ቦታ ያስፋፋ ወይም ማንኛውንም ግንባታ ያካሄደ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአራት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ፲(አስር)ሺ እስከ ፵(አርባ)ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፭/ ያልተፈቀደ የደን ውጤት ያጓጓዘ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር ፭(አምስት)ሺ እስከ ብር ፲(አስር)ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፮/ ማንኛውም የደን ባለቤት በደን ውስጥ ተባይ፣ ተስፋፊነት ያላቸው አረሞችና በሽታ መከሰቱን እያወቀ አግባብ ላለው አካል በአፋጣኝ ያላሳወቀ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር ፩(አንድ)ሺ እስከ ፭ (አምስት)ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፯/ ማንኛውም የደን ባለቤት በደን ውስጥ ያልተፈቀዱ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን ወይም ደቂቅ ነፍሳትን ያስገባ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ፲(አስር)ሺ እስከ ፴(ሰላሣ)ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፰/ ዝርያቸው በመጥፋት የሚገኙ የዛፍ አይነቶችን በህገወጥ መንገድ ከመንግስት፣ ከማህብራት፣ ከማህበረሰብና ከግል ይዞታ ላይ የቆረጠ፣ ያጓጓዘ፣ ያከማቸና ለሽያጭ ያቀረበ ከ፭(አምስት) ዓመት በማያንስና ከ፰(ስምንት) ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከ፲፭(አስራ አምስት) ሺህ ብር እስከ ፳(ሀያ) ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ Any person who intentionally causes damage to a forest by setting a fire or in any other manner shall be punishable with rigorous imprisonment not less than 10 years and not exceeding 15 years; if the damage caused by negligence he shall be punished with simple imprisonment not less than one year and not exceeding two years or with fine Birr 5,000 up to 10,000 Birr.

4/ Any person who settles or expands farmland or undertake the construction in a demarcated forest and forest land shall be punishable with rigorous imprisonment not less than two years and not exceeding four years and fine with from Birr 10,000 up to Birr 40,000.

5/ Any person who illegally moves forest products shall be punishable with simple imprisonment not less than six months and not exceeding one year and with fine from Birr 5,000 up to Birr 10,000.

6/ Any owner of forest who fails to immediately inform the relevant body having the knowledge about the occurrence of forest vermin weeds and disease in his forest shall be punishable with simple imprisonment not less than six months and not exceeding one years and with fine from Birr 1,000 up to Birr 5,000.

7/ Any owner of forest who introduces unauthorized plants, animals and micro organisms shall be punishable with rigorous imprisonment not less than one year and not exceeding three years and with fine from Birr 10,000 up to Birr 30,000.

8/ Any person who cut trees, transport, accumulate and sale forest products illegally from state, association, community, and private forests shall be punished with rigorous imprisonment not less than 5 years and not exceeding 8 years and with fine from birr 15,000 up to birr 20,000

**፳፯. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ደንብ እና መመሪያ እንደ ቅደም ተከተላቸው የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ሚኒስቴሩ ያወጣሉ፤ እንዳስፈላጊቱ ክልሎች ተጨማሪ ደንብና መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፤

**፳፰.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

፩/ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፪/፲፱፻፺፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፱.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**27.<u>Power to Issue Regulation and Directives</u>**

Detailed regulation and directives required for the proper implementation of this Proclamation may be issued by the Council of Ministers and the Ministry, respectively.

**28. <u>Repeals</u>**

1/ The Forest Development, Conservation and Utilization Proclamation No. 542/2007 is hereby by repealed.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect on matters provided for in this Proclamation.

**29. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 23th Day of January 2018.**

**MULATU TESHOME (DR)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**